በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ታቦት - ክፍል ፪

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com

_**ቦታ፡-**_ ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## ታህሳስ ፲፬ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.



# ታቦት…

- **ታቦትን መንካት ወይም መሸከም የሚችሉት ሥልጣነ ክህነት ያላቸው አባቶች ካህናት ብቻ ናቸው፡፡ ክህነት የሌለው ሰው ቢነካው ይቀሰፋል፡፡** “ወደ ናኮንም አውድማ በደረሱ ጊዜ በሬዎቹ ይፋንኑ ነበርና ዖዛ እጁን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን ታቦት ያዘ። የእግዚአብሔርም ቍጣ በዖዛ ላይ ነደደ፥ እግዚአብሔርም ስለ ድፍረቱ በዚያው ቀሠፈው በእግዚአብሔርም ታቦት አጠገብ በዚያው ሞተ። እግዚአብሔርም ዖዛን ስለ ሰበረው ዳዊት አዘነ እስከ ዛሬም ድረስ የዚያ ስፍራ ስም የዖዛ ስብራት ተብሎ ተጠራ።” ***ካል ሳሙ 6:6-8፣ ዘሌ 16:2፣ ኢያ 3:5-17፣ 1ኛ ሳሙ 5:9-12፣ 1ኛ ነገ 8:4፣ ኢያ 6:12፣ ቀዳ ዜና 13:9-11፣ ቀዳ ዜና 15:2፡፡***
- **ለታቦት ክብርና ስግደት ይገባል፡፡** “ሕዝቡም ሁሉ የደመናው ዓምድ በድንኳኑ ደጃፍ ሲቆም ያየው ነበር ሕዝቡም ሁሉ ተነሥቶ እያንዳንዱ በድንኳኑ ደጃፍ ይሰግድ ነበር።” ***ዘጸ 33:10፣ ቀዳ ሳሙ 5:1-5፣ ካል ቆሮ 6:16፡፣ኢያ 7:6፡፡***
- **የቃል ኪዳኑን ታቦት በዕልልታና በጭብጨባ ማጀብ ይገባል፡፡** “የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ሰፈር በገባ ጊዜ እስራኤል ሁሉ ታላቅ እልልታ አደረጉ፥ ምድሪቱም አስተጋባች። ፍልስጥኤማውያንም የእልልታውን ድምፅ በሰሙ ጊዜ። በዕብራውያን ሰፈር ያለው ይህ ታላቅ የእልልታ ድምፅ ምንድር ነው? አሉ። የእግዚአብሔርም ታቦት ወደ ሰፈሩ እንደገባ አስተዋሉ።” ***ቀዳ ሳሙ 4:5-6***
- “ንጉሡ ዳዊትም እግዚአብሔር የአቢዳራን ቤትና የነበረውን ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ታቦት እንደ ባረከ ሰማ። ዳዊትም ሄዶ የእግዚአብሔርን ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ በደስታ አመጣው። የእግዚአብሔርንም ታቦት የተሸከሙ ስድስት እርምጃ በሄዱ ጊዜ አንድ በሬና አንድ ፍሪዳ ሠዋ። ዳዊትም በሙሉ ኃይሉ በእግዚአብሔር ፊት ይዘፍን ነበር ዳዊትም የበፍታ ኤፉድ ለብሶ ነበር። ዳዊትና የእስራኤልም ቤት ሁሉ ሆ እያሉ ቀንደ መለከትም እየነፉ የእግዚአብሔርን ታቦት አመጡ። የእግዚአብሔርም ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ በገባ ጊዜ የሳኦል ልጅ ሜልኮል በመስኮት ሆና ተመለከተች፥ ንጉሡም ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ሲዘልልና ሲዘፍን አየች በልብዋም ናቀችው። የእግዚአብሔርንም ታቦት አገቡ፥ ዳዊትም በተከለለት ድንኳን ውስጥ በስፍራው አኖሩት ዳዊትም የሚቃጠልና የደኅንነት መሥዋዕትን በእግዚአብሔር ፊት አሳረገ። ዳዊትም የሚቃጠልና የደኅንነት መሥዋዕት ማሳረግ ከፈጸመ በኋላ ሕዝቡን በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም መረቀ። ለሕዝቡም ሁሉ ለእስራኤል ወገን ለወንዱም ለሴቱም ለእያንዳንዱ አንዳንድ እንጀራ አንዳንድም የሥጋ ቍራጭ አንዳንድም የዘቢብ ጥፍጥፍ አከፋፈለ። ሕዝቡም ሁሉ እያንዳንዱ ወደ ቤቱ ሄደ። ዳዊትም ቤተ ሰቡን ሊመርቅ ተመለሰ። የሳኦልም ልጅ ሜልኮል ዳዊትን ለመቀበል ወጣችና። ምናምንቴዎች እርቃናቸውን እንደሚገልጡ የእስራኤል ንጉሥ በባሪያዎቹ ቈነጃጅት ፊት እርቃኑን በመግለጡ ምንኛ የተከበረ ነው! አለችው። ዳዊትም ሜልኮልን፦ በእግዚአብሔር ፊት ዘፍኛለሁ በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል ላይ አለቃ እሆን ዘንድ ከአባትሽና ከቤቱ ሁሉ ይልቅ የመረጠኝ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት እጫወታለሁ። አሁንም ከሆንሁት ይልቅ የተናቅሁ እሆናለሁ፥ በዓይንሽም እዋረዳለሁ ነገር ግን በተናገርሽው ቈነጃጅት ዘንድ እከብራለሁ አላት። የሳኦልም ልጅ ሜልኮል እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም።” ***ካል ሳሙ 6:12-15፣ መዝ 134:1-4፡፡***

# ታቦት…

- የክብር ዙፋን የሆነው የታቦት ክብሩ እስከ ዓለም ፍጻሜ በምድር ይቀጥላል፡፡ በምድርም በሰማይም በቤተ መቅደሱ ያለ ታቦቱ ነውና፡፡ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው።" 2ኛ ተሰ 2:4፡፡
- "እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል።" ማቴ 5:17-19 ካል ቆሮ 6:14-16፣ እብ 9:1-22፣ ኢሳ 45:23
- የታቦት ክብር በሐዲስ ኪዳን በሰማይ ታይቷል፡፡ "በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ።" ራዕይ 11:19፡፡
- ታቦት በሐዲስ ኪዳን የባሕርይ አምላክ የንጉሡ ነገሥት የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋውና የደሙ የክብር ዙፋን ነው፡፡ ዮሐ 6:56፡፡
- በታቦቱም ላይ አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው የዘለዓለም አምላክ የሚለው ቅዱስ ስሙ ነው፡፡ በታቦቱ ፊት የሚሰገደውም ለዚህ ቅዱስ ስሙ ነው፡፡ "ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበርከኩ፡፡" ፊል 2:10፡፡
- እስራኤልም በታቦቱ ፊት ስግደት ያቀርቡ ነበር፡፡ "ኢያሱም ልብሱን ቀደደ፥ እርሱና የእስራኤልም ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እስከ ማታ ድረስ በግምባራቸው ተደፉ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ።" ኢያሱ 7:6፡፡

# ታቦት…

- "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የአሕዛብን መንገድ አትማሩ ከሰማይ ምልክትም አትፍሩ አሕዛብ ይፈሩታልና። የአሕዛብ ልማድ ከንቱ ነውና ዛፍ ከዱር ይቈረጣል፥ በሠራተኛም እጅ በመጥረቢያ ይሠራል። በብርና በወርቅ ያስጌጡታል፥ እንዳይናወጥም በችንካርና በመዶሻ ይቸነክሩታል። እንደ ተቀረጸ ዓምድ ናቸው እነርሱም አይናገሩም መራመድም አይቻላቸውማን ይሸከሙአቸዋል። ክፉ መሥራትም አይቻላቸውምና፥ ደግምም መልካም ይሠሩ ዘንድ አይችሉምና አትፍሩአቸው።" ***ኤር 10:2-5፤*** የተገረው ለአሕዛብ ጣዖት ነው፡፡ ለመሆኑ "ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው?" ***ካል ቆሮ 6:16፡፡***
- እስራኤል የቃልኪዳኑን ታቦት ትተው ወደ ጣዖት በመመለሳቸው የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር መጥቶ ኢየሩሳሌምን እንደሚወር፣ ቤተ መቅደሱን እንደሚያፈርስ ንዋያተ ቅዱሳቱም እንደሚዘረፉ፣ ሰባ ዘመን እንደሚማረኩ በባዕድ አገርም የቃልኪዳኑን ታቦት አያገኙትምና የታቦቱን ስም መጥራት አትችሉም ተባሉ፡፡ ይህን የነገራቸውን ነቢይ ኤርምያስንም ሽንት ቤት ውስጥ ከተውታል፡፡ ***ኤር 25:1-11፡፡***
- **ከምርኮም በኋላ ወደ እግዚአብሔር በአንድነት አልቅሰዋል፣ ቤተ መቅደሱን መልሰው አሳንጸዋል… *ኤር 50:1-5፣ ሐጌ 1 እና 2፡፡***
- የመጀመሪያው መቅደስ፣ ታቦት፣ መጽሐፍ … አንድ ነበር፡፡ እንደ አማንያን መብዛት ግን አብያተ ክርስቲያናት ይታነጻሉ፣ ታቦታት ይዘጋጃሉ፣ መጻሕፍትም ይታተማሉ… "ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፥ ንጹሕም ቍርባን ያቀርባሉ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡" ቤቱንም ያጸዳው ለዚሁ ነው፡፡ ***ሚል 1:11፣ ዘጸ 34:1-27፣ ማቴ 21:12-15፡፡***
- "እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።" ***ማቴ 5:23*** "ደግማችሁም። ማንም በመሠዊያው የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በላዩ ባለው መባ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል ትላላችሁ። እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች፥ ማናቸው ይበልጣል? መባው ነውን? ወይስ መባውን የሚቀድሰው መሠዊያው? እንግዲህ በመሠዊያው የሚምለው በእርሱና በእርሱ ላይ ባለው ሁሉ ይምላል፡፡" ***ማቴ 23:19፡፡*** **በማለት በሐዲስም የቀጠለውን የታቦቱን (የመሠዊያውን) አገልግሎት ያመለክተናል፡፡** "ከመሰዊያውም። አዎን፥ ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ፍርዶችህ እውነትና ጽድቅ ናቸው ብሎ ሲናገር ሰማሁ።" ***ራእ 16:7፡፡***
- ሌላው በሐዲስ እግዚአብሔር አምላክ ራሱን ለዓለም የገለጠባት ታቦት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ናት፡፡

ይቀጥላል…

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡